*የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)*
*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

## <u>የፓርቲው 45ኛ ዓመት በዓለ ክብር</u>

**ጳጉሜ 4 ቀን 2009 <u>ዓም</u>**

## <u>የተከበራችሁ ወገኖቻችን !</u>

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐብዮታዊ ፓርቲ/ኢሕአፓ የተመሰረተበትን 45ኛ ዓመት በዓል እንድናከብር ጥሪያችንን አክብራችሁ ስለመጣችሁ ከልብ የመነጨ ምስጋናችንን አናቀባለን ። እንኳን ደህና መጣችሁ !

ፓርቲው ከተመሰረተ ፤ ግማሽ ምዕተ-ዓመት እየሆነው ነው ። በየካቲት 66 ዓም ዐብዮት ዋዜማ ፤ ኅልውናውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበሰረው ኢሕአፓ ፤ሀገራችን የነበረችበት ተጨባጭ ሁኔታ፤ እንዳችም የፖለቲካ ድርጅት ያልነበረባት ስለነበርች ፤ የፓርቲው መፈጠር ፤ ለኢትዮጵያ አዲስ ክስተት ነበረ ። በሀገር ውስጥ የሚንቀሳቀስ ሌላ ፖለቲካዊም ሆነ ሕዝባዊ ድርጅት ባለመኖሩ ምክንያት ፤ሀገራዊ ተመክሮና ልምድ ሊቀስም የሚችልበት ፓርቲው አንዳችም ዕድል አልነበረውም ። ከዚህም በቀር፤ ተደራጅቶ የመንቀሳቀስም ይሁን ኃስብን በነፃ ለመግለፅ የሚያስችል የዴሞክራሲ መብትና ነፃናት ፍንጭ እንኳን አልነበረም ። በዚኽ ምክንያት ሁሉንም ጉዳይ ባዲስ መልክ ሀ ብሎ መጀመር ነበረበት። ፓርቲው ሲመሰረት፤ ዋነኛ ዓላማ አድርጎ የተንሳው፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከነበረችበት እጅግ ኋላቀር አሳሳቢ ደረጃና የከፋ አስተዳደር በደል አላቅቆ፤ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመላው ሀገሪቱ እንዲሰፍን የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማድረግ ነበር ።

ፓርቲው ሲመሰረት፤ ታላቅና ታሪካዊት የሆነችው ሀገራችን፤ ነፃናቷን፤ ሀገራዊ ልዋላዊነቷን፤ የዜጎቿን ዕኩልነትና ነፃነት ጥብቃ በመቀጠል፤ በዴሞክራሲ ሥርዓት እየተመራች ወደ ልማትና ብልጽግና መራመድ አለባት የሚል ስትራተጃዊ ራዕይ ነበረው።

ይህንን የሩቅ ራዕይ አንግቦ ሲነሳ ፤ ጊዜው የየካቲት የ1966 ዓም ሕዝባዊ ዐብዮት ዋዜማ ነበር ። ማንም ያለጠበቀውና ያልተዘጋጀበት ዐብዮት ስለነበር፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ዕንግዳ ደራሽ ሆኖ መጣበት/ለት። ዐብዮቱ፤ መሪና አቅጣጫ ሰጭ በማጣቱም፤ ፓርቲው በለጋ ዕድሜው ከባዱን ኃላፊነት ለመሸከም ወደ ኋላ ሊል አይጠበቅበትምና፤ በዚያ ታሪካዊና ቀውጢ ሰዓት፤ ሕዝቡን ለማደራጀት ወገንተኝነቱን አስመሰከረ ። ሕዝቡም፤ ዐብዮቱ ያመጣለትን ዕድል በአግባቡ እየተጠቀመ የዴሞክራሲ መብቱን ተጎናፅፎ የሥልጣን ባለቤትነቱን እንዲያረጋግጥ ፤ ፓርቲው የተቻለውን ጥረት ሁሉ ሲያደርግ ቆይቷል።

ይኽንንም ለማሳካት፤ ከመላው የሀገሪቱ ኅብረተሰብ የተውጣጣ ጊዚያዊ የመሸጋገሪያ ወቅት ሊኖር አስፈላጊ እንደነበረ በአፅናኦትና በድፍረት ተናገረ። ይኽንን ለመናገር የሚያስችለው፤ ታሪካዊና መሠረታዊ ምክንያቶች ነበሩት። እነርሱም የሀገራችን ተጨባጭ ባኅላዊ፤ ፖለቲካዊ፤

ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎች ናቸው። ዕጅግ ሲበዛ ኀልታዊ የሆነ ኅታች መንግሥታዊ አስተዳደርና ኋላ ቀር በሆነ ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማትን ድልዳል ያደረገ ኢፍትሃዊ ኖሩን የሚያስተናግድ ሥርዓት ነበር ።፡ፍትኀ-ርትዕ የጎደለው ብቻ ሳይሆን፤ የሃይማኖት፤ የብሄርና የጾታ ልዩነቶችና ከአንገፍጋፊ ደረጃ በላይ ነበሩ። የየካቲት ዐብዮት ይኸንን የሀገሪቱ ምስቅልቅል ሁኔታ ሁሉ አካትቶ ለማስተናገድ፤ በግድ ጊዚያዊ የሽግግር ሂደት መካሄድ እንደነበረበት ፓርቲው በተገቢው መንገድ ተገንዝቦ ይፋ አድርጎ አሳወቀ። በአጭሩ፤ ፊውዳላዊቷ ሀገር ኢትዮጵያ፤ በግድ የሽግግር ወቅት ሂደት ማለፍ አማራጭ አልነበረውም ።

ይኸንን መሠረታዊ ምክንያትና አስገዳጅ ጊዜ የማይሰጥ አጣዳፊ ክንዋኔ በተግባር ለመለወጥ በግድ የሕዝብ ሙሉ ተባባሪነትና ንቁ ተሳትፎ እንዲመጣ ከማድረግ የተሻለ ሌላ አማርጭ አልነበረም። የሀገሪቱ ኅልውና ሳይናጋ፤ የዜጎቿ አንድነት ሳይበውዝ፤ የጠላቾቿም ምኞት እንዳይሳካ ማድረግ ፤ የፓርቲው ስትራተጂያዊ ዓላማ ስለነበር፤ የዴሞክራሲ ሥር ዓት መስፈን ምንም ሌላ አማራጭ ያልነበረው ብቸኛ አማራጭ ነበር ። ይኸንን ባለ ሩቅ ራዕይ አመለካከት፤ ለሥልጣን የቋመጡ ጥቂት ወታደሮችና ተባባሪዎቻቸው ሊቀበሉት ስለአልፈለጉ፤ አጥብቀው ተቃወሙት።

ሕዝብ ቢደራጅ የሚያስከትልባቸውን ተቃውሞ አስቀድመው በመገንዘባቸው፤ የሕዝቡን ዴሞክራሲያው ጥያቄዎች ሁሉ አፍነው፤ አምባገነን አገዛዝን አስፍነው በአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ እያስፈራሩ፤ ዐመተ-ፍዳና ጽልመተ ምጽዐት በመለዋ ሀገራችን ላይ ዘረጉ ። ኢትዮጵያዊውን ሕዝባዊ ዐብዮት ነጥቀው፤ ለባዕዳን መጠቀሚያ አሳልፈው ሰጡት። የኢትዮጵያንም ሕዝብ ድል ነጠቁ። ሕዝቡን ካዱት/ ከዱት ! ፀረ- የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆናቸውንም በአደባባይ አረጋገጡ።

ኢትዮጵያ ሀገራችንም፤ በአንድ ቀን ጀምበር የደርግ ዐዋጅ ፤ ከአረጀ -አፈጀ ንጉሣዊ አገዛዝ ወደ ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ተሸጋገረች ። እነኝህ ከየጦር ሰፈራቸው ተጠራርተው የመጡ ለሥልጣን ያቋመጡ ስብስቦች፤ ሁለተኛውን ዙር የፈላጭ-ቆርጭ ፋሽስታዊ ዐዋጅ በማወጅ፤ ሀገሪቱ አሁን ለደረሰችበት አዘቅት የመሰረት ድንጋይ አስቀመጡ። ሕዝቡም ከማያቋረት ፍዳና አበሳ ውስጥ ገብቶ የኸው፤ ለአለፉት አምሣ ዓመታት የቁም-ስቃዩን ያያል ። ዛሬ፤ ሀገሪቱም በመኖርና ባለመኖር መካከል ትገኛለች።

በሥልጣን ማቋመጥ ላይ ብቻ የተመሠረተ አገዛዝና ሥርዓተ መንግሥት፤ የሀገሪቱና የሕዝቧ ዕጣ ፋንታ፤በመጨረሻው ምን አዘቅት ውስጥ ጥሎት እንደሚሄድ፤ ኢትዮጵያ ሀገራችን እንደ መጥፎ ምሣሌ መቆጠሯ ፤ ዜጎቿን እያሳዘናቸው መሆኑን መገንዘቡ፤ ኢሕ አፓን ያበሳጨዋል ። እነኝህ የሥልጣን ጥመኞች ከመጀመሪያውኑም ቢሆን ፤ ለሀገር - ለወገን እንደማይጠቅሙ ፤ ፓርቲው መስማት ለሚፈልገው ሁሉ አስቅድሞ ተናግሯል። አሁን ላይ ፤ይኸንን ሲል፤ እኔ፤ " **አስቀድሜ ተናግሬ ነበር**" በማለት ራስን የማወድስ አባዜንና የነብይነትን ባኅርይ ለማሳየት ሳይሆን፤ የነበረውን ዕውነታ ለማስታወስና አሁን ሀገሪቷ የገጠማትን ሁኔታ ለማስገንዘብ ብቻ መሆኑን መግለፅ እንፈልጋለን ።

የየካቲቱ ዐብዮት ወደ አደገኛ አቅጣጫ እየሄደ መሆኑን አስቀድሞ በመረዳት፤ የደርግን አገዛዝና አጫፋሪዎቹን በግንባር ቀደም የተቃወማቸውን ኢሕ አፓን የጥቃታቸው ዒላማ አደረጉት ። የደርግ አሽቃባጮችና ተላላኪዎቹም አብረው ሊያጠፉት ተራባረቡበት። አቅሙ

የሚፈቅድለትን ሁሉ እያደረገ ጥቃታቸውን ሁሉ ተከላከለ። ፓርቲውን ሊያጠፈት ያሴሩትን ተንኮል ሁሉ አከሸፈባቸው።

የኢትዮጵያን ኅልውና ፤ ዓይነተኛና ብቸኛ ጠባቂና ተቆርቋሪ መሆኑን በመርዳታቸው ገንጣዮችና አስገንጣዮች ሁሉ ሳይቀሩ ተባበሩበት። የደርግ አፈቀላጤዎችና ሰይፈ-ጃግሬዎችም ተራቸውን ጠብቀው የአፍላ ጊዚያቸው ሲያከትም እነርሱም ራሳቸው የደርግ ሰለባ ሆነው ቀሩ። ደርግም ቢሆን፤ መውደቁ የጊዜ ጉዳይ ስለነበር፤ ሂደቱን ጨርሶ ራሱም ጠፋ ። ችግሩ ግን ፤ የደርግ መጥፋት ሳይሆን፤ ሀገሪቱን አጥፍቶ፤ ማክተሙ ነበር። የደርግ አጥፍቶ መጥፋት ፤ ጠንቁ ለሀገርና ለወገን መትረፉ ግን አይቀሬ ነበረና ያ መሆኑ ፓርቲውን አላስገረመውም። ወያኔም በተራው የደርግን እጣ -ፋንታ እነደሚያገኝ ፤ የአምባገነኖች የቆየ ታሪክ ይመስክራል ። ያም ቢሆን ግን፤ የሀገራችን ሕዝብ የትግል ታሪክ እስካሁን ያስመዘገበው፤ አምባገነኖችን ማስወግድን እንጅ ፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መተካት አልነበርም ። አሁንም ቢሆን፤ የአምባገንን አገዛዝ፤ በዴሞክራሲ ሥርዓት የሚተካበት ሂደትና ጥረት ካልተጀመረ፤ የሀገራችን ሁኔታ ከመከራና ስቃይ አዙሪት ሊወጣ አይችልም ። ፓርቲው አዙሪቱ እንዲሰበር የተቻለውን ሁሉ ከማድረግ አይታብይም ።

እስካሁን ድረስ፤ ፓርቲው ፤ ሁሉንም እንዳመጣጣቸውና እንደ ሁኔታው ተቆቁሞ አልበገሬ ኢትዮጵያዊ ኃይል መሆኑን በተግባር አስመሰከሯል። የዚህ ሁሉ ጥንካሬ ዓብነትና ምሥጢር ፤ የፓቲው የአመሰራረት ራዕይና ዓላማ፤በቋሚ ዕምነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ነው። የአደረጃጀት ስልቱም በወቅቱ፤ የተራቀቀ እንደነበር፤ እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ባላንጣዎቹም የመሰከሩት ሀቅ ነው። የአባላቱ ተአውፃኦም የኢትዮጵያን ግራማሴነት አንፀባራቂ ነበር።

አባላቱ፤ ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የተወለዱና የተውጣጡ፤ በመሆናቸው፤ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን በዕኩልነት የሚያዩ፤ የሚያስተናግዱ ፤ ሉሁሉም ነፃነትና ዕኩልነት ፤ ዕድገትና ብልፅግና ብሎም ፤ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚታገሉ ስለነበሩ፤፤ ሁለንተናዊ ሰብዕናን የተላበሱ ሆነዋል። በዚህ ምክንያት፤ የሁሉንም ዜጋ ድጋፍና ዕምነትን አትርፈዋል ። ለዚህ የተከበረ ዕምነት ሲሉም አይከፍሉ መሥዋዕት እየከፈሉ ፤ ሕዝባዊ ታማኝነታቸውን፤ አስመስጋኝ ታሪክ በመስራት አስመስክረዋል ።

" **ለትግል መሞት ፤ ዘለዓለማዊ ሕይውት!** " እያሉ ዘለዓለማዊ ክብርን ተጎናፅፈው አልፈዋል ። ፓርቲው 45ተኛ ዐመት በዐሉን ሲያከብር ፤ መሥዋዕታዊ አባላቱን እያከበረ ብቻ ሳይሆን፤ የተሰውበትን ዓላማ በማንገብ፤ ቃል ኪዳኑንም እንዳገና አድሶ፤ ትግሉን የሚያፋፍም መሆኑንም ጭምር በኩራትና በልበ-ሙሉነት እየገለፀም ነው። ይዚኽ ቃል ኪዳን ተሃድሶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሞራል እያገነባ የጠላቶቹንም ቅስም እንደሚሰብር ጠርጥር አኖርም !

የኢሕአፓ ታጋዮች፤ ሕዝባቸውን ፤ በዘርና በቋንቋ፤ በሃይማኖትና በነገድ መከፋፈል ፤ ያዛዝናቸዋል። ያስቆጣቸዋል፡፤ ያናድዳቸዋል። በመሆኑም እስከመጨረሻው ድረስ ይታገሉታል ። የኢትዮያን ሕዝብ ፤ በአጥንት ፍላጭ፤ በደም ጭላጭ፤ በነገድ ብጥስጣሽ መከፋፈል አይቻልም። የትግሬ ወያኔዎች ይኽንን እያደረጉ ዓላማቸውን ለማሳካት ይፍጨረጨራሉ። ግን ፈፅሞ

አይሳካላቸውም። ይኸንን መርዘኛና ዘረኛ አገዛዝ ሕዝቡ ፤ አጥብቆ እየተቃወመው ይገኛል ። ኢሕአፓ ዛሬም ፤ እንደ ትላንቱ ፤ ሕዝባዊነቱን ከወገኑ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ቆሞ ጠላቱን ይፋለመዋል። ፓርቲውና ሕዝቡ በአካልና መንፈስ በተየያዘ የአንድነት ቀል ኪዳን ስለተዋሃዱ ፤ ኢትዮጵያ ከመጥፋቷ በፊት፤ ፓርቲው ፤ ብርቱ መሥዋዕት ለመክፈል ይገደድ ይሆናል እንጅ፤ ሀገራችን ግን አትጠፋም ። ይኸ የዕምነት ቃል፤ለበዐል ከባበር ፍጆታ እንዲሆን የተቀመረ ሳይሆን፤ ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ የሆነ ዘለዓለማዊ የኢሕአፓ ዕምነት እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል ።

የጀመሩትን ክቡር ሀገራዊ ትግል በመካድ ፤ ወደየብሄራቸው የሄዱት ይታዘንላቸዋል እንጅ አይታዝንባቸውም። ምክንይቱም፤ የኋላኋላ ፤ ዘለዓለማዊቷ ኢትዮጵያ ፤ዘለዓለም መቀጥሏ ስለሚቀጥል፤ በጋራ ሀገራችን አብረን እንደምንኖር እናውቃለን። ይኸ በመሆኑ፤ በዘር ፖለቲካ የተበከለቱ ሁሉ፤ ከጥፋታቸው ታርመው ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን በሚደረገ ው ትግል እንዲሰለፉ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። ወደ ኢትዮጵያ ጎራ ኑ፤ ተሰልፉ እንላቸዋለን !

## <u>ኸቡራትና ክቡራን ዕንግዶቻችን !</u>

ዛሬ ሀገራችን፤ በአንድ ዘረኛ አምባገንን አገዛዝ ስር ወድቃለች ። ኢትዮጵያ በረዥም ታሪኳ ፤ እንደዚህ ያለ የመከፋፈል አደጋ አላጋጠማትም ። የሀገር ጥፋትና የሕዝብ መከፋፈል ጥቃት ወንጀል አልተዘነዘረባትም ። የዚህ ወንጀል ተጠያቂ፤ የትግሬው ወያኔ ቡድን ነው። ዘርንና፤ ቋንቋን መስፈርት ያደርገ የጭቆና ቀምበር ወድቆባታል። በመርዝ የተደቆሰ አደገኛ ክፍፍል ለዘመናት አብሮ የኖረውን ሕዝብ ተለያይቶ በጠላትነት እንዲተያይ ሊያደርጉት እየሞከሩ ነው ።

በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች፤ የውጭ ባዕዳን የሀገራችንን ኅልውና ለመፈተታን የተለያዩ ዘዴዎችን ቢጠቀሙም፤ የሁሉንም ተንኮል፤ ሕዝቡ እንዳመጣጣቸው እየመከተ አከሽፏቸዋል ። ሀገራችንንም ለተተኪው ትውልድ እያስረከበ በክብር አልፏል። ያሁኑ ሁኔታ ግን የተለየ ነው። የውጭ ባዕድን ጠላቶች ሳይሆኑ፤ ሀገር- በቀል የሆኑ የውስጥ ጠላቶች ናቸው። ሀገር በቀል ሆነው፤ የባዕዳንን ዓላማ የሚያስፈጽሙ መሰሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባላንጣዎች ናቸው። ቱርኮች፤ ጣሊያኖችና እንግሊዞች፤ ሀገራችንን በቋንቋና በሃይማኖት ከፋፍለው፤ ቅኝ ግዛት ለማደርግ ሞክረው ያልተሳካላቸውን፤ ዛሬ፤ የትግሬ ወያኔዎች ስኬታማ ለማድረግ እየተፍጨረጨሩ ይገኛሉ።

የኤርትራን ሕዝብ፤ ከወንድሙ ከኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲለያይ አድርገዋል። ሀገሪቱንም የባኅር በር አሳጥተዋታል ። ሕዝባችን ዛሬ በበለጠ የሚያዝነው ግን፤ የባኅር በር ማጣቱ ብቻ ሳይሆን፤ ከወንድሙ ከኤርትራ ሕዝብ ጋር በግድ እንዲለያይ በመደረጉም ጭምር ነው። ይኸንን መሠረታዊ ሃቅ ፤ አስተዋዩ የኤርትራ ሕዝብ የሚስተው አይደለም ።

በወያኔ ስር የወደቀችውን ሀገር ሁለንተናዊ ችግሩች ዘርዝረን አንጨርሰውም ።ከሞላ ጎደልም ቢሆን ሁሉም ዜጋ ያውቀዋል ብለን እናምናለን ። የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግሮችና የተጋረጠባትን አደገኛ መርዝ ኢሕ አፓ ብቻውን የፈታዋል የሚል ብዥታ የለም። ሁሉም ከተባበረ ግን በአጭር ጊዜ ሊፈታ ይችላል ብሎ ያምናል ። የኅብረትን አስፋልጊነትና ወሳኝነት አስቀድሞ በመረዳቱ ሁሉንም ያካተተ ትግል እንዲሳካ የተቻለውን ሁሉ ሲያደርግ ቆይቷል። ይኸ ጥረቱ፤ በታሪክ የተመዘገበ ስለሆነ፤ ወደ ዝርዝር መግባቱ፤ ለጊዜው አስፋላጊ ባይሆንም፤ ለታሪክ

ማስታዎሻ ከጠቀመ ግን፤ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ኃይሎች ቅንጅትንና ( ኢዴኃቅ ) የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ( ኢዴኃኅ) ን መጥቀስ በቂ ነው።

ይኽንን የኅብረት ጥረት ለታሪክ ገመገማና ፍርድ ትተን፤ አሁንም እንደገና በአዲስ መልክ ፤ አዲስ የኅብረት ጥሪ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ፤ ፓርቲው ያለመሰልቸት ተመሳሳይ ዓላማና ግብ የኖራቸዋል ከሚባሉት ጋር የኅብረት ትግል ለማድረግ ፤ ያለመሰልቸት ጥሪ ሲይደርግ ቆይቷል ፡፡ ዛሬም ፤ ይኸው የ45ተኛ በዐሉን ሲያከብር በታላቅ ተስፋ የኅብረት ጥሪውን ያስተላልፋል። አውንታዊ መልሳቸውንም በጉጉት ይጠብቃል ። በዚኽ በዐላችን የተገናችሁ ወገኖቻችንም፤ ይኽንን የፓርቲውን የኅብረት ጥሪ አስፈላጊነትና አንገብጋቢነት ተረድታችሁ፤ የበኩላችሁን፤ የተባብሩ መልዕክታችሁን ለአንድነት ኃይሎች እንድታስተለልፉ በትኅትና እንጠቃችኋለን !

በዐላችንን ለማክበር ስለተገኛችሁልን በድጋሚ እናመስግናል ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም በነፃነቷ ትኑር !